# ትምህርት 33

1. እግዚአብሔር ከሚነድድ ቁጥቋጦ ውስጥ ሙሴን ሲያነጋግረው የገባለት ቃል ምን ነበር?

*ሀ- እግዚአብሔር ሙሴን መልሶ ወደ ሲና ተራራ እንደሚያመጣው ቃል ገብቶለት ነበር።*

2. እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ሲና ተራራ እንደሚመልሰው የገባለትን ቃል ጠብቆአል?

*ሀ- አዎን።*

3. እግዚአብሔር በተራራ ጫፍ ላይ ሙሴን ምን አለው?

*ሀ- እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር ቃል ኪዳን ማድረግ እንደሚፈልግ ነገረው።*

4. እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር ማድረግ የፈለገው ቃል ኪዳን ምን ነበር?

*ሀ- እግዚአብሔር እስራኤላውያን የእርሱን ትእዛዛት ሁሉ ቢጠብቁ እንደሚባርካቸው ተናገረ።*

5. እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ ባይጠብቁ እግዚአብሔር ምን ያደርጋቸዋል?

*ሀ- ይቀጣቸዋል።*

6. ከዚያስ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ምን አሉ?

*ሀ- የእግዚአብሔር ትእዛዛት ሁሉ እንደሚጠብቁ ገለጹ።*

7. እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ መጠበቅ እንደሚችሉ አስበው ነበር?

ሀ- አዎን።

8. እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ መጠበቅ እንደሚችሉ ያሰቡት ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም ትእቢተኞችና እምቢተኞች ስለ ነበሩ ነው።

9. እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ መጠበቅ ችለው ነበር?

ሀ- አልቻሉም።

10. እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ መጠበቅ ያልቻሉት ለምን ነበር?

ሀ- የአዳምና የሔዋን ልጆች ሆነው ስለ ተወለዱ ነው።

ለ- የኃጢአት ባሪያዎች ሆነው ስለ ተወለዱ ነው።

ሐ- የሰይጣን ባሪያዎች ሆነው ስለ ተወለዱ ነው።

11. እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ መጠበቅ እንደማይችሉ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር?

ሀ- አዎን።

12. ታዲያ እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ መጠብችቅ እንደማይችሉ እያወቀ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን ማድረግ የፈለገው ለምንድን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር ቃል ኪዳን ማድረግ የፈለገው እስራኤላውያንን ሊያስተምራቸው ነበር።

13. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ሊያስተምራቸው የፈለገው ምን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር እስራኤላውያን የእርሱን ትእዛዛት ሁሉ መጠበቅ እንደማይችሉ እንዲያውቁ ሊያስተምራቸው ፈለገ።

ለ- እግዚአብሔር እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ መጠበቅ በጭራሽ የማይችሉት በኃጢአት ስለ ተወለዱ መሆኑን ሊያስተምራቸው ፈለገ።

ሐ- እግዚአብሔር እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ መጠበቅ በጭራሽ ስለማይችሉ እግዚአብሔር ብቻ ከዘላለም ሞት ሊያድናቸው እንደሚችል ሊያስተምራቸው ፈለገ።

14. እስራኤላውያን የሲናን ተራራ ከነኩ የሚሞቱት ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር በተራራው ላይ ይወርድ ስለነበር ነው።

ለ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ነው።

ሐ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ ስለሚጠላ ነው።

መ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት ስለሚቀጣ ነው።

15. ነጐድጓድ መብረቅ ጢስና እሳት የምን ምልክቶች ነበሩ?

ሀ- እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን የሚያመለክቱ ነበሩ።

ለ- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ እንደሚጠላ የሚያመለክቱ ነበሩ።

ሐ- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት እንደሚቀጣ የሚያመለክቱ ነበሩ።

- ከእግዚአብሔር ጋር ከተነጋገረ በኋላ ሙሴ ወደ ተራራው ግርጌ ተመለሰ።

- ነጐድጓዱ በተራራው አጠገብ ሰማዩን አናውጦት ነበር።
- መብረቁ በተራራው ዙሪያ ያለውን አየር ሞላው።

- ጥቅጥቅ ያለ ጢስ ተራራውን ሙሉ በሙሉ ሸፍኖት ነበር።
- ተራራው በሙሉ በኃይል መናወጡን ቀጠለ።

- እስራኤላውያን እጅግ ፈርተው ስለነበር፥ ከተራራው ራቅ ብለው ነበር።

- ከዚያም እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከተራራው ላይ ሆኖ ተናገራቸው።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በሲና ተራራ ምን ሰጣቸው?
- አሥርቱን ትዕዛዛት፤

ዘጸአት 20፥1-2

1- እግዚአብሔር እነዚህን ቃሎች ሁሉ እንዲህ ብሎ ተናገረ፤
2- «ከግብፅ ባርነት ምድር ያወጣሁህ አምላክህ እኔ ነኝ።»

- እግዚአብሔር የሰጠው የመጀመሪያ ትእዛዝ እንዲህ የሚል ነበረ፥

ዘጸአት 20፥3

3- «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑርህ።»

- በመጀመሪያው ትእዛዝ እርሱ ብቻ አምላካችን ሊሆን እንደሚገባው እግዚአብሔር አዟል።

- እግዚአብሔር ብቻ አምላካችን መሆን ያለበት ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም አምላክ አንድ ብቻ ስለ ሆነ ነው።

- ምክንያቱም ሌላ አምላክ ስለሌለ ነው።

- ወደ መናፍስት በምንጸልይበት ጊዜ መናፍስትን ከእግዚአብሔር ማስበለጣችን ነው። በዚህም ይህንን የእግዚአብሔር ትእዛዝ አፈረስን ማለት ነው።

- በድግምት ስንታመን ድግምትን ከእግዚአብሔር ማስቀደማችን ነው።

በዚህም ይህን ትእዛዝ አፈረስን ማለት ነው።

- ከእግዚአብሔር መንገድ ይልቅ በራሳችን መንገድ ስንሄድ ራሳችንን ከእግዚአብሔር አስበለጥን ማለት ነው። በዚህም ይህን ትእዛዝ አፈረስን ማለት ነው።

- እግዚአብሔር አምላካችን እንዲሆን በማንፈቅድበት በእያንዳንዱ ቀንና ሰዓት፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አፈረስን ማለት ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ይህን ትእዛዝ አፍርሰዋል ይላል።

- ይህን ትእዛዝ ማፍረስ የሚያስከትለው ቅጣት ሞት ነው። ይህም በዘላለሙ የእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

- እግዚአብሔር የሰጠው ሁለተኛው ትእዛዝ ይህ ነው፡

ዘጸአት 20፡4-5

4- «በላይ በሰማይ ወይም በታች በምድር ካለው ወይም በውኃ ውስጥ ከሚኖሩት ነገሮች በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖትን አታብጅ።

5- አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም፤ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ የሚጠሉኝን ልጆች ከአባቶቻቸው ኃጢአት የተነሣ እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ድረስ የምቀጣ ቀናተኛ አምላክ ነኝ።»

- በሁለተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር ምንም ዓይነት የእንጨትም ሆነ የድንጋይ ምስል እንዳንሠራ ወይም እንዳናመልካቸው አዝዞናል።

- በእግዚአብሔር አምሳል ምስል መሥራት የሌለብን ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር መንፈስ ስለ ሆነ ነው።

- እግዚአብሔር ሰውን እንስሳን ወይም ወፍን አይመስልም።

- ከእግዚአብሔር ይልቅ እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ነገሮች ስናመልክ እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ነገሮች ከእግዚአብሔር አስቀደምን ማለት ነው። በዚህም ይህን ትእዛዝ አፈረስን ማለት ነው።

- በእያንዳንዱ ቀንና ሰዓት እግዚአብሔርን የማናመልክ ከሆነ የየራሳችንን ወይም የሌሎችን አሳብ የምንከተል ከሆነ ይህን ትእዛዝ አፍርሰናል ማለት ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ይህን ትእዛዝ አፍርሰዋል ይላል።

- ይህን ትእዛዝ ማፍረስ የሚያስከትለው ቅጣት ሞት ነው። ይህም በዘላለሙ የእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

- እግዚአብሔር የሰጠው ሦስተኛው ትእዛዝ ይህ ነው፡

ዘጸአት 20፡7

7- «የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም ያለ አግባብ አታንሣ፤ እግዚአብሔር ስሙን ያለ አግባብ የሚያነሣውን በደል አልባ አያደርገውምና። »

- በሦስተኛው ትእዛዙ የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ እንዳንጠራ እግዚአብሔር አዞናል።

- የእግዚአብሔርን ስም ማክበር ያለብን ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም የእግዚአብሔር ስምና እግዚአብሔር ስለማይነጣጠሉ ነው።
- ምክንያቱም የእግዚአብሔር ስምና እግዚአብሔር አንድ ስለሆኑ ነው።

- የእግዚአብሔርን ስም በአክብሮት የማንጠራ ከሆነ እግዚአብሔርን አላከበርነውም ማለት ነው፤ በዚህም ይህን ትእዛዝ አፈረስን ማለት ነው።

- የእግዚአብሔርን ስም በግድየለሽነት ስንጠራ እግዚአብሔርን በግድየለሽነት ነው የምንቀርበው፤ በዚህም ይህን ትእዛዝ አፈረስን ማለት ነው።

- ልጁ ታላላቆቹን አለማክበሩ መጥፎ ነገር ነው።
- አንድ ሰው እግዚአብሔርን ባያከብር በጣም መጥፎ ነገር ነው።
- እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ይህን ትእዛዝ አፍርሰዋል ይላል።

-ይህን ትእዛዝ ማፍረስ የሚያስከትለው ቅጣት ሞት ነው። ይህም በዘላለሙ የእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

- እግዚአብሔር የሰጠው አራተኛው ትእዛዝ ይህ ነው፡-

ዘጸአት 20፡8-11

8- «የሰንበትን ቀን ቅዱስ አድርገህ አክብር።

9- ስድስት ቀን ትሠራለህ፤ ሥራህንም ሁሉ አከናውን።

10- ሰባተኛው ቀን ግን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ሰንበት ነው። በዕለቱ አንተም ሆንህ ወንድ ልጅህ ወይም ሴት ልጅህ፤ ወንድ አገልጋይህ ወይም ሴት አገልጋይህ፤ ወይም እንስሳትህ ወይም በደጅህ ያለ መጻተኛ ምንም ሥራ አትሠሩም።

11- እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ባሕርንና በውስጡም ያሉትን ሁሉ በስድስት ቀን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፎአል። ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባረከው፤ ቀደሰውም።»

- በአራተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን ልዩ የዕረፍት ቀን አድርገን እንድንጠብቀው አዘዘን።

- በሳምንት አንድ ቀን ማረፍ ያለብን ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን በስድስት ቀን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ስላረፈ ነው።

- እግዚአብሔር እኛም በሰባተኛው ቀን እንድናርፍ ያዘዘን አርፈን እርሱ ለእኛ ስለ ፈጠራቸው ነገሮች እንድናስብ ነው።

- ካላረፍንና ስለ እግዚአብሔር ካላሰብን ይህን ትእዛዝ አፍርሰናል ማለት ነው።

- ካላረፍንና እግዚአብሔር የሠራልንን ሁሉ ካላሰብን ይህን ትእዛዝ አፍርሰናል ማለት ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ይህን ትእዛዝ አፍርሰዋል ይላል።

- ይህን ትእዛዝ ማፍረስ የሚያስከትለው ቅጣት ሞት ነው። ይህም በዘላለሙ የእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

- እግዚአብሔር የሰጠው አምስተኛው ትእዛዝ ይህ ነው፡-

ዘጸአት 20፡12

12- እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም። አባትህንና እናትህን አክብር፤

- በአምስተኛው ትእዛዝ አባቶቻችንና እናቶቻችንን እንድናከብር እግዚአብሔር አዝዞናል።

- አባቶቻችንንና እናቶቻችንን ማክበር ያለብን ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እኛን እንዲያሳድጉ እግዚአብሔር እነርሱን ስለሰጠን ነው።

- አባቶቻችንን ሙሉ በሙሉ የማንታዘዝ ከሆነ ይህን ትእዛዝ አፈረስን ማለት ነው።

- እናቶቻችንን ሙሉ በሙሉ የማንታዘዝ ከሆነ ይህን ትእዛዝ አፈረስን ማለት ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ይህን ትእዛዝ አፍርሰዋል ይላል።

- ይህን ትእዛዝ ማፍረስ የሚያስከትለው ቅጣት ሞት ነው። ይህም በዘላለሙ የእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

- እግዚአብሔር የሰጠን ስድስተኛ ትእዛዝ ይህ ነው፡

ዘጸአት 20፡13

13- «አትግደል።»

- በስድስተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር ሰውን እንዳንገድል አዝዞናል።

- ሰውን መግደል የሌለብን ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ለሰዎች ሁሉ ሕይወትን የሰጠው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነና መውሰድም የሚችለው እርሱ ብቻ ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር እንዳለው አንድን ሰው ከጠላነው ምን አደረግን ማለት ነው?

- እግዚአብሔር አንድን ሰው ከጠላነው እንደገደልነው ተናግሮናል።

- ሌሎች ሰዎችን ከጠላን ይህንን ትእዛዝ አፈረስን ማለት ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ይህን ትእዛዝ አፍርሰዋል ይላል።

- ይህን ትእዛዝ ማፍረስ የሚያስከትለው ቅጣት ሞት ነው። ይህም በዘላለሙ የእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

- እግዚአብሔር የሰጠን ሰባተኛው ትእዛዝ ይህ ነው፡

ዘጸአት 20፡14

14- «አታመንዝር።»

- በሰባተኛው ትእዛዝ ከሕጋዊ ባለቤታችን ውጭ ከሌላ ጋር እንዳንተኛ (የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳንፈጽም) ታዝዘናል።

- ከሕጋዊ ባለቤታችን ውጭ ከሌላ ጋር መተኛት የሌለብን ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር አንድን ወንድ ለአንዲት ሴት አንዲትን ሴት ለአንድ ወንድ ነው የሰጠው።

- እግዚአብሔር እንዳለው ወንድ ሴትን አይቶ፥ ሴትም ወንድን አይታ አብረው ለመተኛት ከተመኙ ምን አደረጉ ማለት ነው?

- እግዚአብሔር እንዳለው ወንድ ሴትን አይቶ፥ ሴትም ወንድን አይታ አብረው ለመተኛት ከተመኙ ያን ጊዜ አመነዘሩ ማለት ነው።

- ከእኛ ተቃራኒ ጾታ ያላቸውን ሰዎች ተመልክተን ከእነርሱ ጋር ለመተኛት ብንፈልግ ይህንን ትእዛዝ አፍርሰናል ማለት ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ይህን ትእዛዝ አፍርሰዋል ብሏል።

- ይህን ትእዛዝ ማፍረስ የሚያስከትለው ቅጣት ሞት ነው። ይህም በዘላለሙ የእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

- እግዚአብሔር የሰጠው ስምንተኛ ትእዛዝ ይህ ነው፡-

ዘጸአት 20፡15

15- «አትስረቅ።»

- በስምንተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር እንዳንሰርቅ አዝዞናል።
- የሌሎችን ንብረት መስረቅ የሌለብን ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር ንብረት የማፍራት መብት ስለሰጣቸው ነው።

- እግዚአብሔር የአንድን ሰው ንብረት ለመስረቅ ካሰብን ምን አደረግን አለ?

- እግዚአብሔር የአንድን ሰው ንብረት ለመስረቅ ካሰብን እንደሰረቅን ተናግሯል።

- የአንድን ሰው ንብረት ከተመለከትንና ለመስረቅ ከፈለግን፥ ያን ጊዜ ይህን ትእዛዝ አፈረስን ማለት ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ይህን ትእዛዝ አፍርሰዋል ይላል።

- ይህን ትእዛዝ ማፍረስ የሚያስከትለው ቅጣት ሞት ነው። ይህም በዘላለሙ የእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

- እግዚአብሔር የሰጠው ዘጠነኛው ትእዛዝ ይህ ነው፦

ዘጸአት 20፥16

16- «በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር።»

- በዘጠነኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር እንዳንዋሽ አዝዞናል።
- መዋሸት የሌለብን ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ውሸት ከእግዚአብሔር አይደለም።
- ምክንያቱም ውሸት ከኃጢአትና ከሰይጣን ነው።

- እግዚአብሔር እውነትን እያወቅን የማንናገር ከሆነ ምን እያደረግን ነው አለ?

- እግዚአብሔር እውነትን እያወቅን የማንናገር ከሆነውሸታሞች ነን ብሏል።

- እግዚአብሔር እውነትን እያወቅን የማንናገር ከሆነ ውሸታሞች ነን ይህንም ትእዛዝ አፈረስን አለ።

- እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ይህን ትእዛዝ አፍርሰዋል ይላል።

- ይህን ትእዛዝ ማፍረስ የሚያስከትለው ቅጣት ሞት ነው። ይህም በዘላለሙ የእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

- እግዚአብሔር የሰጠን አሥረኛው ትእዛዝ ይህ ነው፤

ዘጸአት 20፡17

17- «የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት ወይም የእርሱን ወንድ አገልጋይ ሆነ ሴት አገልጋይ በሬውንም ሆነ አህያውን ወይም የእርሱ የሆነውን ማናቸውንም ነገር አትመኝ።»

- በአሥረኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር ሌሎች ሰዎች ያሏቸውን ነገሮች እንዳንመኝ አዝዞናል።

- የሌሎችን ንብረት መመኘት የሌለብን ለምንድን ነው?
- ለሌሎች ያላቸውን ነገር የሰጣቸው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

- ሌሎች ያላቸውን ነገር ስንመኝ ይህን ትእዛዝ እናፈርሳለን።
- እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ይህን ትእዛዝ አፍርሰዋል ይላል።

- ይህን ትእዛዝ ማፍረስ የሚያስከትለው ቅጣት ሞት ነው። ይህም በዘላለሙ የእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጣቸው አሥርቱ ትእዛዛት እነዚህ ናቸው።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጣቸው እነዚህ ትእዛዛት ለሰዎች ሁሉ የተሰጡ ናቸው።

- ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ መፈጸም አይችልም።
- እኛ ሁላችንም የእግዚአብሔርን ትእዛዛት አፍርሰናል።

- ሁሉንም ትእዛዛት እየጠበቁ አንዷን እንኳን ስለመተላለፍ እግዘብሔር ምን አለ?

- እግዘብሔር ሁሉንም ትእዛዛት እንደ መተላለፍ ነው አለ።

- ዐሥርቱን የእግዚአብሔር ትእዛዛት አለመጠበቅ የሚያስከትለው ቅጣት ምንድን ነው?

- ሞት ይኸውም በዘላለማዊ የእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

- አንዷን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብቻ መጣስ ምንን ያስከትላል?

- ሞትን ይኸውም በእሳት ባሕር ውስጥ መጣልን።

- እግዚአብሔር ሰይጣንን ከሰማይ ከመወርወሩና የእሳት ባሕር ለእርሱ ከማዘጋጀቱ በፊት ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ያመፀው ስንት ጊዜ ነበር?

- አንድ ጊዜ ብቻ።

- ሰይጣን ኃጢአት የሰራው አንድ ጊዜ ቢሆንም ቅጽበት እግዚአብሔር የሞት ፍርድ ፈረደበት።

- እግዚአብሔር ከሰማይ አውጥቶ ወደ ተዘጋጀላቸው የእሳት ባሕር እነርሱን ከመጣሉ በፊት ሰይጣንን የተከተሉት ክፉ መላእክት ስንት ጊዜ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላለፉ?

- አንድ ጊዜ ብቻ

- ሰይጣን የተከተሉት መላእክት ኃጢአት የሰሩት አንድ ጊዜ ብቻ ቢሆንም እግዚአብሔር የሞት ፍርድ ፈረደባቸው።

- አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር ከዔድን የአትክልት ስፍራ ሳያባርራቸው በፊት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የተላለፉት ስንት ጊዜ ነበር?

- አንድ ጊዜ ብቻ።

- አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የተላለፉት አንድ ጊዜ ብቻ ቢሆንም እግዚአብሔር በሞት ቀጣቸው።

- እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ አንድም ኃጢአት ቢሆን እንኳ በሞት መቀጣት አለበት።

- የእግዚአብሔር ትእዛዛት ልክ እንደ መስተዋት ናቸው።

- የእግዚአብሔር ትእዛዛት እንደ መስተዋት የሆኑት እንዴት ነው?
- የእግዚአብሔር ትእዛዛት ኃጢአታችንን እንድናይ ስለሚያግዙን ነው።
- የእግዚአብሔር ትእዛዛት ኃጢአታችንን ስለሚያሳዩን ነው።

- እግዚአብሔር ትእዛዛቱን ለምን ሰጠን?

- ቆሻሻውንና ኃጢአተኛውን ልባችንን እንዲያሳዩን።

- አንድ ሰው ያለመስታወት የቆሸሸውን ፊቱን ማየት እንደማይችል ሁሉ በእግዚአብሔር ትእዛዛት አማካይነት ካልሆነ የቆሸሸውንና ኃጢአተኛውን ልባችንን ማየት አንችልም።

- እግዚአብሔር ትእዛዛቱን ለእስራኤላውያን የሰጣቸው ቆሻሻና ኃጢአተኛውን ልባቸውን ለእስራኤላውያን ሊያሳያቸው ነበር።

- እግዚአብሔር ትእዛዛቱን የሰጠው ለሰዎች ሁሉ የቆሸሸውንና ኃጢአተኛውን ልባቸውን ሊያሳያቸው ነው።

- ልባችን የቆሸሸና በኃጢአት የተሞላ (የረከሰ) በመሆኑ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ምንም ዓይነት ነገር ማድረግ አንችልም።

- ልባችን የቆሸሸና ኃጢአተኛ በመሆኑ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን ለማግኘት ምንም ነገር ማድረግ አንችልም።

- ቆሻሻውንና ኃጢአተኛውን ልባችንን ፈጽሞ ማንጻት አንችልም።

- የቆሸሸውንና ኃጢአተኛውን ልባችንን ማንጻት የሚችለው ማን ብቻ ነው?

- እግዚአብሔር ብቻ ነው።